

*የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ቋሚ*
*መልዕክተኛ ጽ/ቤት*
*ጀኔቫ*
*Permanent Mission of Ethiopia to the United Nations*
*and Other International Organizations*
*Geneva*

# ዜና መጽሔት

# Newsletter

*ቁጥር 1* *የካቲት 1999 ዓ.ም*


## ኢትዮጵያ በሶማሊያ የወሰደችው እርምጃ ከዓለም አቀፍ ህግ አኳያ

የኢትዮጵያ መከላከያ ሃይል በሶማሊያ እስላማዊ ፍርድ ቤቶች ታጣቂ ሃይሎች ላይ የወሰደው እርምጃና ያስገኘው ውጤት በዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ዘንድ ሰፊ ተቀባይነት ያገኘ ነው:: ውጤቱ ለ15 ዓመታት ማዕከላዊ መንግስት ሳይኖራት ለፀረ-ሰላምና ለአክራሪ አሸባሪዎች ጥላ ከለላ ሆና ለቆየችው ሶማሊያ ወደ ሠላማዊ የፖለቲካ ሥርዓት እንድትመለስ ሁኔታዎችን አመቻችቷል:: ከብዙ ጥረትና ከረዥም ጊዜ ድርድር በኋላ ተመስርቶና በባይደዋ ተቀምጦ የነበረው የሶማሊያ የሽግግር መንግስት በሞቃዲሾና በሌሎችም የአገሪቱ ክልሎች መዋቅሩን መዘርጋት እንዲጀምር ዕድል ሰጥቶታል:: በአጠቃላይም ውጤቱ ሶማሊያን እርግፍ አድርጎ ትቶ የነበረው ዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ሶማሊያን የመርዳት ፍላጎቱ የመነሳሳት ምልክቶች ታይተውበታል:: ውስን ኢኮኖሚያዊ አቅም ያላት ኢትዮጵያ ይህን ካደረገች ሌላውም የራሱን ድርሻ መወጣት ይኖርበታል የሚል አስተሳሰብ ፈጥሯል::

ከውጤቱ አኳያ ሠፊ ተቀባይነትና ድጋፍ ያገኘው የኢትዮጵያ ሚና ከዓለም አቀፍ ህግ አኳያም ተገቢና ትክክለኛ ነበር:: ኢትዮጵያ በመስራች አባልነቷ የፈረመችው የተባበሩት መንግስታት ቻርተር አንቀጽ 51 ማንኛውም አባል አገር ከጥቃት ራሱን የመከላከል መብት እንዳለው ይደነግጋል:: ቻርተሩ የአገሮች ራስን የመከላከል መብት የማይገሰስ የተፈጥሮ መብት (inherent right) እንደሆነ ያረጋግጣል::

የእስላማዊ ፍርድ ቤቶች ህብረት በኢትዮጵያ ላይ ጥቃት ለማድረስ ግልፅና ተደጋጋሚ የጦርነት አዋጆችን ሲያደርግ ቆይቷል::

በኢትዮጵያ ላይ የጂሃድ ጦርነት እንዲካሄድም ጥሪውን አስተላልፏል:: የእስላማዊ ፍርድ ቤቶቹ አመራሮች ከዚህም አልፈው የሶማሊኛ ተናጋሪ ኢትዮጵያውያን የሚገኙበትን ክልል በሃይል ለመቆጣጠር እርምጃ እንደሚወስዱ በይፋ ተናግረዋል:: በነዚህ አዋጆቹ መሠረትም የእስላማዊ ፍርድ ቤቶቹ ታጣቂዎች በመደበኛና በሙያዊ ግዴታቸው ላይ በነበሩት በኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት አባላት ላይ ተደጋጋሚ የጥቃት እርምጃዎችን ወስደዋል:: እነዚህ ጥቃቶች በኢትዮጵያ ወገን እንደክስ የቀረቡ ሳይሆኑ በጥቃት ፈጻሚዎቹ በራሳቸው ወገን የተነገሩና ማስረጃም የሚያስፈልጋቸው አልነበሩም::

በእርግጥ ራስን የመከላከል መብት የማይከለክለው ዓለም አቀፍ ህግ በተለይም የተመድ ቻርተር ችግሮችን ለመፍታት ለሰላማዊ መንገድ ቅድሚያ እንዲሠጥ ይጠይቃል:: በዚሁ መሠረት ከዚህ በላይ የተመለከቱት የእስላማዊ ፍርድ ቤቶች የጦርነት አዋጆችና ጥቃቶች ሲፈጸሙ በኢትዮጵያ ወገን የእስላማዊ ፍርድቤቶቹን አመራሮች በመቅረብና ለውይይት በመጋበዝ አለ የተባለው ችግር በውይይት እንዲፈታ ተደጋጋሚ ጥረቶች ተደርገዋል:: ነገር ግን ግንኙነቱ በተደረገ ቁጥር «ምላሻችንን ወደፊት እንሰጣለን» እያሉ በመሬት ላይ ጥቃታቸውን ቀጠሉ:: በመሆኑም ከእስላማዊ አክራሪዎቹ ጋር በውይይት ለመግባባት ምንም አይነት እድል እንደሌለ ግልጽ ሆነ::

የእስላማዊ ፍርድቤቶቹ ታጣቂዎች በኢትዮጵያ የመከላከያ ሃይል እርምጃ ሲወሰድባቸውና ወደ መሃል ሶማሊያ እየሸሹ ባሉበት ሁኔታ እንኳን የሰላም ንግግር እንዲጀመር አልጠየቁም:: ወደ ደቡባዊ ሶማሊያ እየሸሹ ተመልሰው መጥተው ውጊያቸውን እንደሚቀጥሉ ያውጁ ስለነበር፤ የኢትዮጵያ መከላከያ ሃይልም የሶማሊያን ሉዓላዊነትና ነጻነትን በመድፈር ሳይሆን፤ ታጣቂ ሃይሎቹን ለማባረር፤ ከተቻለም አላማቸውን በሃይል ማግኘት እንደማይችሉ ሲረዱ ወደ ድርድር ጠረጴዛ እንዲመጡ ለማስቻል ሲል ወደ መሃልና ደቡባዊ ሶማሊያ ሊዘልቅ ችሏል::

ስለዚህም ኢትዮጵያ ከእስላማዊ ፍርድ ቤቶች የተሰነዘረበትን ጥቃት ተከትሎ የወሰደችው ምላሽ ከዓለም አቀፍ ህግ አኳያ ሲታይ ሙሉ በሙሉ ተገቢና ትክክለኛ ነበር:: ይህም በመሆኑ ውሳኔው ከአንድ የአፍሪካ አገር ፕሬዝዳንት (አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ) በስተቀር ጉዳዩን በተቃውሞ አይን የተመለከተው የለም:: በጉዳዩ ላይ ዓለም አቀፍ ሃላፊነቱ ያለበትና የተመድ የጸጥታው ምክር ቤትም የኢትዮጵያ መንግስት የወሰደው እርምጃን አስመልክቶ፤ አንድ ስብሰባ በማድረግ ከተነጋገረበት በኋላ በአዎንታዊነት ተመልክቶት ማለፉ አካሄዱ ህጋዊነትን የተከተለ መሆኑን ያረጋግጣል:: በአፍሪካ ደረጃ የሰላምና ፀጥታ ጉዳዮችን የመከታተል ሃላፊነቱ ያለበት የአፍሪካ ህብረትም በሰጠው ምላሽ ኢትዮጵያም ትሁን ሌላ አገር ራሱን የመከላከል መብቱ የተጠበቀ መሆኑን ገልጾ ለኢትዮጵያ እርምጃ አዎንታዊ ሃሳቡን ገልጿል::

ከተባበሩት መንግስታት ቻርተር ህግ ሌላ በልምድ ከሚታወቀው ዓለም አቀፍ ህግ (Customary International Law) አኳያም ቢሆን፤ የኢትዮጵያ መንግስት ውሳኔን ህጋዊነት ማስረዳት ይቻል ነበር:: በዚህ ልማዳዊ ህግ መሠረት አንድ አገር ጦርነት ሳይታወጅበትም ወይም የሃይል እርምጃ ሳይወሰድበትም በፊት፤ ከድንበሩ ባሻገር በሚገኝ ኃይል የወረራ ዛቻና ማስፈራራት ሲደረግበት፤ የጥቃት ዝግጅት እየተደረገለት እንደሆነ ምልክቶች (imminent attack) መኖራቸው ሲገነዘብ፤ ያ ቡድን በሃይል ድንበሩን ተሻግሮ እስኪመጣ ሳይጠብቅ እራሱን የመከላከል እርምጃ (anticipatery self defense) መውሰድ ይችላል:: ይህ ልማዳዊው ዓለም አቀፍ ህግ መሠረት የሚያደርገው ሊካሄድ የነበረን ወረራ ቀድሞ ማክሸፍንና የሌላውን አገር ሉዓላዊነት የመድፈር ዓላማ የሌለ መሆኑን ግልጽ ማድረግ ነው::

ኢትዮጵያ በእስላማዊ ፍርድ ቤቶች ጦርነት በይፋ ታውጆባታል:: ቡድኑ ተዋጊ ሃይሎቹንም ቀስ በቀስ በኢትዮጵያ ድንበር አካባቢ ሲያጠናክርና ሲያስጠጋ ቆይቷል:: የጦር መሳሪያ ፍላጎቶቹንም ለማሟላት በአውሮፐላኖች ሲያጓጉዝ እንደነበረ ታውቋል:: በህጋዊው የሶማሊያ የሽግግር መንግስት ጋባዥነት በባይደዋ የነበሩና የሽግግር መንግስቱን የጸጥታ ሃይሎች አቅም ግንባታ ስልጠና ላይ የነበሩ የኢትዮጵያ የመከላከያ ኃይል ኦፊሰሮች ከባይዶዋ ካልወጡ የሃይል እርምጃ እንደሚወሰድባቸው በይፋ ተናግሯል:: እነዚህ ሁሉ ድርጊቶች የኢትዮጵያ መንግስት በአለም አቀፍ ህጉ መሠረት እራሱን የመከላከል ምላሽ እንዲሠጥባቸው ያስችሉት ነበር:: ይሁንና የኢትዮጵያ መንግስት ከላይ ለተመለከቱት ግልጽ አደጋዎች(imminent attack) በዚህ ህግ መሠረት ምላሽ ከመስጠት ይልቅ ራስን እያዘጋጁ መቆየትን መርጧል:: በመሠረቱ የኢትዮጵያ መንግስት ይህንን ህግ መሠረት ያደረገ እርምጃም እንደሚወስድ የገለጸበት ወይም የወሰደበት ሁኔታ የለም::

በአጠቃላይም የእስላማዊ ፍርድቤቶቹ የጦርነት ዛቻዎቻቸውን ተግባራዊ ለማድረግ ታጣቂዎቻቸውን ድንበር አሻግረው ጥቃት መፈጸም በመጀመራቸው፤ የኢትዮጵያ መንግስት ምላሽ ተገቢነቱና ህጋዊነቱ ከተመድ ቻርተር አኳያ ብቻ ማየቱ በቂ ይሆናል:: ስለዚህም የኢትዮጵያ መንግስት በሶማሊያ የወሰደው እርምጃ ከውጤቱ አኳያ ብቻ ሳይሆን ከህጋዊነት አኳያም ተገቢነቱ አጠያያቂ አይሆንም::

# በስዊትዘርላንድ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ቅኝት

ኢትዮጵያውያን በስዊትዘርላንድ መኖር ከጀመሩ አያሌ ዓመታት አስቆጥረዋል:: በስዊትዘርላንድ ነዋሪ ኢትዮጵያውያን እና በትውልድ ኢትዮጵያውያን እንደሌሎቹ አውሮፓ አገሮች ብዛት ያላቸው ባይሆኑም ከአገሪቱ የቆዳ ስፋትና ህዝብ ብዛት አንጻር አነስተኛ ነው ማለት አይቻልም::

በስዊዘርላንድ ነዋሪ ኢትዮጵያውያን በተመለከተ መሠረታዊ መረጃ ለማሰባሰብ በተጠናው ጥናት መሠረት እ.ኤ.አ እስከ ዲሴምበር 2005 ዓ.ም. ድረስ ባለው መረጃ በስዊዘርላንድ ባጠቃላይ 3,571 ነዋሪ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ይገኛሉ:: እነዚህ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን በተለያዩ የአገሪቱ ካንቶኖች የሚኖሩ ሲሆን በስዊዘርላንድ የመኖሪያ ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት መሠረት 405 ኢትዮጵያውያን በቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ ወይም (Permee C)፤ 589 ኢትዮጵያውያን በየዓመቱ የሚታደስ የመኖሪያ ፈቃድ (Permee B) 1,568 ኢትዮጵያውያን ለስዊዝ መንግስት የጥገኝነት ጥያቄ አቅርበው ጥያቄያቸው ውድቅ የሆነባቸው ወይም የጥገኝነት ጥያቄ በፍርድ ቤት ወይም በስዊዝ ኢሚግሬሽን ቢሮ በመታየት ላይ የሚገኝ ወይም (Permee F ወይም N ) ያላቸው ናቸው:: ቀሪዎቹ 1,009 ኢትዮጵያውያን የስዊዝ ዜግነት ያላቸው ትውልድ ኢትዮጵያውያን ናቸው::

ይህ መረጃ በስዊዘርላንድ ከሚገኙ ከሌሎች አገሮች ዜጎች አንጻር ለመቃኘት ብንሞክር በስዊዘርላንድ ነዋሪ ከሆኑ የውጭ ዜጎች 0.16% ኢትዮጵያውያን ሲሆኑ፤ ስዊዘርላንድ ከሚገኙ 26 ካንቶኖች የሚኖሩ የውጭ ዜጎች አንጻር ትላልቅ ከተሞች ብንመለከት ዙሪክ 0.12%፤ በርን 0.26%፤ ጄኔቭ 0.33% ፤ ሎዛን 0.15%፤ ኢትዮጵያውያን ነዋሪዎች ናቸው::

በስዊትዘርላንድ ነዋሪ ኢትዮጵያውያን ከአገራቸው ጋር ያላቸውን ትስስር በማጠናከር በኢንቨስትመንት፤ በReal Estate,፤ በትራንስፖርት ዘርፍ፤ በቡና ማምረት፤ በአስመጪነት (Importer)፤ በሰብዓዊ እርዳታ እና የኢትዮጵያ ወጪ ምርቶችን በማሻሻጥ የሚያበረታታ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ናቸው:: በተጨማሪም በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በአገራቸው የመኖሪያ ቤት መገንባት እንዲችሉ በተሰጠው ዕድል መሠረት እስካሁን 160 በስዊዘርላንድ ነዋሪ ኢትዮጵያውያን በ10 ማህበራት ተደራጅተው የመኖሪያ ቤት ግንባታ የቦታ ጥያቄ አቅርበው መልስ በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ::

መንግስት በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በአገራቸው የልማት እንቅስቃሴ ተሳታፊ በመሆን ራሳቸውንና አገራቸውን እንዲጠቅሙ ከማንኛውም ጊዜ በበለጠ ለመደገፍና ለማበረታታት ተቋማዊ ማስተካከያዎች በማድረግ ውጭ ነዋሪ ኢትዮጵያውያን ችግሮችን መከታተል የሚያስችል አሠራርና አደረጃጀት ፈጥረዋል::

## ዜና

### የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሚለንየም በሚል ለማክበር ለሚመጡ በቂ ዝግጅት የአየር ትራንስፖርት ለማቅረብ እየተዘጋጀ ነው::

የኢትዮጵያ ሚለንየም በዓል ለማክበር ወደ ኢትዮጵያ ለሚመጡ ኢትዮጵያውያንና የውጭ አገር ዜጎች በቂ የአየር ትራንስፖርት ለማቅረብ መንገዶችን ለማጓጓዝ የሚበርባቸው ከተሞች ተጨማሪ ምልልሶች ለማድረግ አስፈላጊ ዝግጅት በማጠናቀቅ ላይ መሆኑ ገለጸ::

አየር መንገዱ ለዚህ በግል ሁለት ቦይንግ 767 አውሮፕላኖች በመከራየት በሚያዝያና ሰኔ ወር ላይ ወደ አገር ውስጥ እንደሚያስገባ ይፋ አድርገዋል::

ኢ.ዜ.አ

## አዲሱ የኢትዮጵያ ሚሊንየም የአፍሪካ ሚሊንየም ተብሎ በደመቀ ሁኔታ እንዲከበር የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ ጥሪ አቀረበ::

አዲሱ የኢትዮጵያ ሚሊንየም የአፍሪካ ሚሊንየም ተብሎ በደመቀ ሁኔታ እንዲከበር የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ ጥሪ ማቅረቡ ተገለጸ:: በመጭው ዓመት በዓለም ላይ ብቸኛ የሆነውና ኢትዮጵያ የምታከብረው ሚሊንየም የአፍሪካ አገሮች ህዝቦች የራሳቸው አድርገው በመቀበል ከኢትዮጵያ ጋር በመሆን በደመቀ ሁኔታ እንዲያከብሩት ጥሪ አቅርበዋል::

## ኢትዮጵያ ከአሥሩ ቀዳሚ የቱሪስት መዳረሻዎች አንዷ እንደሆነች ይፋ ተደረገ::

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ በ2007 ከአስሩ ቀዳሚ የቱሪስት መዳረሻዎች አንዷ እንደሆነች ፍሮመርስ ትራቭልጋይድ የተሰኘውን የጉብኝት ፕሮግራም በኢንተርኔት የሚያስተዋውቅ ድርጅት ይፋ ማድረጉን የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር አስታወቀ::

ሚኒስቴሩ ባወጣው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ ድርጅቱ የጉብኝት ፕሮግራም ለማድረግ ለሚሹ ተጓዦች የተሟሉ መረጃዎችን በማቅረብ በዓለም ላይ በቀደምትነት የሚጠቀስ ሲሆን ለያዝነው የፈረንጆች ዓመትም ከተለያዩ የጉዞ መጽሐፍትና ኤክስፐርቶች የተገኙ መረጃዎችን በማሰባሰብ የአስር ቀዳሚ የቱሪስት መዳረሻዎችን ምርጫ አካሂዷል::

በዚህም መሠረት ኢትዮጵያ ዘመናትን ካስቆጠረ የርስ በርስ ጦርነት በመላቀቅ አዲስ የልማት መስመር ቀይሳ መንቀሳቀስ መጀመሯና የተሻሻለውም የመሠረተ ልማት ግንባታ ለአገር ውስጥ ዝውውር ምቹ ሁኔታ በመፍጠሩ ጉብኝት ለማድረግ ለሚሹ ቱሪስቶች ሁኔታዎች መመቻቸቱን ድርጅቱ ጠቅሷል::

ለዚሁ ተመራጭነት ኢትዮጵያ የያዘቻቸው በርካታ መስህቦች ከፍተኛውን እገዛ እንዳደረጉ ሚኒስቴሩ ገልጿል:: በመሆኑም በ2007 ጉብኝት ለማድረግ የሚሹ ሁሉ ሊያይዋት የሚገባ አገር ናት ተብላ መመረጧን አመልክቷል::

ፎሮመርስ ትራቭል ጋይድ ላለፉት 50 ዓመታት ያህል በመላው ዓለም ስለሚገኙ የቱሪስት መዳረሻዎች ግልጽና ተአማኒነት ያላቸውን መረጃዎች በማሰራጨት የሚታወቅ አንጋፋ ድርጅት መሆኑንም ሚኒስቴሩ ጨምሮ ገልጿል::

## በግንባርና በዲፕሎማሲው መድረክ የተመታው የሻዕቢያ የሽብር ሙከራ ዳግም መምከኑ ተገለጸ::

በግንባርና በዲፕሎማሲው መድረክ የተመታው የሻዕቢያ የሽብር ሙከራ ዳግም መምከኑን የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎትና የፌዴራል ፖሊስ የፀረ ሽብር ግብረ ኃይል አስታወቁ::

የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎትና የፌዴራል ፖሊስ የፀረ-ሽብር ግብረ ኃይል «ሽብርን ከምንጩ የማድረቅ ጥረታችን ያሳካል!» በሚል ለኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት በላኩት መግለጫ እንዳመለከቱት የአፍሪካ ኅብረት መዲና የሆነችው አዲስ አበባ ሰሞኑን የአህጉሪቱን መሪዎች፤ የተመድ ዋና ጸሐፊ፤ የአውሮፓ ኅብረት ባለሥልጣናት፤ የአረብ ሊግ ከፍተኛ ተወካዮችና የተለያዩ የዓለም አገራት ከፍተኛ ተወካዮች የተካፈሉበትን ስብሰባ እጅግ በሚያረካ መልኩ አስተናግዳለች:: ለዚህም የኢትዮጵያ ሕዝቦች ብቻ ሳይሆኑ መላው አፍሪካውያን ኮርተውበታል፤ ደምቀውበታል::

በደቡብ ሶማሊያ መሸጎ በሻዕቢያ አዝማችነት፤ በዓለም ዓቀፍ የሽብርተኞች መረብ ጋሻ ጃግሬነትና ኦነግና ኦብነግን በመሳሰሉ አገር በቀል ሽብርተኞች ተላላኪነት በእስላማዊ ፍርድ ቤቶች ኅብረት አክራሪ ሽብርተኛ ክንፍ ኢትዮጵያ ላይ የተቃጣው ጥቃት በሶማሊያ መንግሥትና በኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት መብረቃዊ እርምጃ ተመትቶ በመከነበት ማግስት በተካሄደው የአፍሪካ ኅብረት ስብሰባ ላይ የኤርትራ መንግሥት አሸባሪነት ገሃድ መውጣቱን አስታውቀዋል::

የህብረቱን ይህ ስብሰባን ጨምሮም የሻዕቢያ መንግሥት ከአፍሪካና ከዓለም ሠላማዊ መንግሥታት መሰል የጋራ መድረኮችና ሂደቶች ተገልሏል ያለው መግለጫው ይህ በፈጠረበት ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ብቸኝነት በመናወዝም የእውር ድንብር ለመንፈራገጥ የተገደደበት ሁኔታ ውስጥ ተዘፍቆ ይገኛል ብሏል::

ከዚህ በመነጨም እነሆ ይህንኑ በድምቀት የተከናወነውን የአፍሪካ ሕብረት ስብሰባ ለማጨናገፍ ብሎም የእንግዶቹን ደህንነት አደጋ ላይ ለመጣል፤ በሻዕቢያ ከፍተኛ ኃላፊዎች ቀጥተኛ አመራር ሰጪነትና በሻዕቢያ የፈንጂ ሙያተኞች ቀጥተኛ ተሳታፊነት አዲስ አበባ ውስጥ ሊፈፀም ታቅዶ የነበረ የሽብር ጥቃት ሙሉ በሙሉ መክሸፉን ይፋ አድርጓል::

ይህ የሻዕቢያ የቀቢፀ ተስፋ ሙከራ የአፍሪካ ሕብረት ስብሰባ ከመካሄዱ አስቀድሞ ዝግጅት ሲደረግበት የቆየ ቢሆንም ከፍተኛ ትዕግስትን ተላብሶ ከተካሄደው የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት የሰከነ ሙያዊ ክትትልና እይታ ውጪ ለአፍታም ቢሆን አላመለጠም ሲል መግለጫው አስታውቋል::

ይልቁንም ተቋሙ ይህንኑ ክትትል በግብዓትነት ተጠቅሞ ሙከራው በምንም ደረጃ ዕድል ሳያገኝ ከህብረቱ ስብሰባ መጀመር በፊት እንዲከሽፍ የሚያስችሉ ሙያዊ እርምጃዎችና ተግባራት በጥንቃቄ ግን ውጤታማ በሆነ መልኩ በመውሰድ የተመቻቸ ሁኔታን መፍጠሩንም ገልጿል::

በዚህም መሠረት በህብረቱ ስብሰባ ዋዜማ በሙሉ፤ የዚሁ ሽብር ዋነኛ አቀናባሪዎች፤ ጥቅም ላይ ሊውሉ ተዘጋጅተው የነበሩ ፈንጂዎች ከእነ ማቀጣጠያዎቻቸውና ሌሎችም ተያያዥ ቁሳቁሶች ከነበሩበት ሁሉ ተለቅመው በቁጥጥር ሥር መዋላቸውንም ይፋ አድርጓል::

ይህም ኢትዮጵያውያን ሠላማዊ ዜጎች በአጠቃላይና በተለይም የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ባደረጉት ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዲሁም በፖሊስና በፀጥታ ኃይሎች ብቃትን የተላበሰ ፈጣን እንቅስቃሴ ሊከናወን የቻለ ደማቅ ድል እንደሆነም አመልክቷል::

የሽብር ቅንብሩንና አቀናባሪዎቹን ዝርዝር መረጃ፤ ማንነትና ሁኔታ የሚመለከት መግለጫ በመጪዎቹ ቀናት ውስጥ ለሕዝብ በይፋ እንደሚቀርብ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎትና የፌዴራል ፖሊስ የፀረ-ሽብር ግብረ ኃይል ባወጡት መግለጫ አስታውቀዋል::

## የተለያዩ መረጃ የሚገኙባቸው ድህረ-ገጾችና አድራሻዎች

- የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
  **www.mfa.gov.et**
- የኢትዮጵያ ሚሽን ጄኔቫ
  **www.ethiopianmission.ch**
- የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ
  **www.ethioinvestment.org**
- አዲስ አበባ ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን
  **www.investaddis.org**
- የሚሊንየም ካውንስል ጽ/ቤት
  **www.ethiopia 2000.com**
- የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
  **www.mofaed.org**

## የኢትዮጵያ አየር መንገድ የጉዞ ወኪሎች

Ethiopian
የኢትዮጵያ

- **AVIAREPS**
  **AIRLINECENTER**
  **Airline Management GMBH**
  **1-3,rue de Chantepoulet**
  **CH-1201 Geneve**
  **Tel (++41 22 ) 919 89 99**
  **Fax (++41 22 ) 919 89 00**
  **e-mail: mélie.kocher@gva.airlinecenter.ch**

- **Christina König Airline Center**
  **Badenerstrasse 15**
  **8004 Zurich,Switzerland**
  **Tel +41 44 286 99 00**
  **Mob + 41 79 688 04 45**
  **Fax + 41 44 286 99 00**
  **e-mail: christina.koenig@zrh.airlinecenter.ch**
  **www.aviareps.com**

## የኢትዮጵያን ቴሌቪዥን

## (ETV)

## ስርጭት ሞገድ

**ETV Parametre**
**12520 MHz**
**Vertical Poliritation**
**27500 symbol Rate**
**FEC3/4**
**ARAB SAT 2D or 3A**

## ማሳሰቢያ

የዜና መጽሄታችን አስተያየት ለመስጠት ወይም ጽሁፍ (Article) ለማበርከት የምትፈልጉ በአድራሻችን በፖስታ ወይም በሚስዮኑ ኢ-ሜይል እንድትልኩልን እየጠየቅን ለማስተናገድ ዝግጁ መሆናችንን እንገልጻለን::

## አድራሻችን

- በተባበሩት መንግስታት የኢትዮጵያ ቋሚ መልዕክተኛ ጽ/ቤት ጄኔቫ::

  **Permanent Mission of Ethiopia to the United Nations Geneva.**

  **56 Rue de Moillebeau**
  **P.O.Box 338, 1211 Geneva 19**
  **Tel (++41 22 ) 919 70 10**
  **Fax (++41 22 ) 919 70 29**
  **e-mail:- info@ethiopianmission.ch**
  **www.ethiopianmission.ch**

